<u>እናት ዓለም ማዘር</u>




ከጥንት ከጠዋቱ
ሲዘረጋ መሠረቱ
የትግል ሰንሰለቱ
ድርብ ነው ጭቆናሽ
ብለው ቢያወሱልሽ
አንዱን ለመታገል
　　ሌላውን የፈታሽ
　　ፆታን አሸንፈሽ
　　ለሀገር የታገልሽ
　　የግል ኑሮ ትተሽ
　　ትግል ቤቴ ያልሽ
　　ዕድሜሽን የሰዋሽ
እናት ዓለም ማዘር
የታጋይ ጓዳ በር።

በጫካው በዱሩ እኩል ተሰልፈሽ
ልጆቼ ተነሱ! ብለሽ አሰልፈሽ
ሰርገሽ መሃላቸው
ብርታትን ስትሰጪ ብለሽ
　　“በለው! በለው!
　　ከቶም እንዳትለቀው!
　　ባንዳ መሠሪ ነው
　　በሀገር የመጣ የሁሉም ጠላት ነው”።
ዜማዊ ቅላፄሽ ትግሉን እያሞቀው
ስንቱን አሰለፍሽው
ብርታት አጉርሰሽው።

እናት ዓለም ማዘር
የታጋይ ጓዳ በር።

ታሪክሽን ጽፈሽ
ጀግንነትን ሰርተሽ
ጀግና ልጅ የወለድሽ
ዕድሜ መስተዋት ነው እንኳንስ አየንሽ።
እናት ዓለም ማዘር
የታጋይ ጓዳ በር።
አንቺ ያሲምባ ጀግና
የኢሕአፓ ቃና
እስቲ ጀባ በይን ትግሉ ይፈላና።
እንትፍትፍ በይብን
እንዳበባ ፈክተን
እንዲሞቅ ቤታችን።

እናት ዓለም ማዘር
የታጋይ ጓዳ በር።

ታሪክሽ ኩራት ነው
የሚሰጥ ብርታት
ሚረጭ ትኩሳት
የተዳፈነ እሳት
እፍ ይበሉት ሴቶች ሁሉም እንዲሞቁት
ተመክሮ ብስራት
አርሃያ ሕይወት።

እናት ዓለም ማዘር
የታጋይ ጓዳ በር።

ትግል አያረጅም በርችሊን አንቺ ጀግና
ከራሩንም ቃኚው ይመታ በገና
ድምጽሽን አሰሚ በይና ልጆቼ
ልምጣ ወደ ቤትሽ ዳገቱን ወጥቼ።
ማዘር እናት ዓለም
　　ኩራት ነው ሕይወትሽ
　　ፍቅር ነው ብስራትሽ
　　አርሃያ ጽናትሽ
ዕድሜ በዕድሜ ላይ በረከት ይሁንሽ።
እኛስ ኮራን ባንቺ
　　ማዘር እናት ዓለም
ሞቅ ይበል ቤታችን ዝምታን አይወድም
አልፋ ኦሜጋ ነው ትግላችን ዘላለም።
በርቺልን ኑሪልን እናት ዓለም ማዘር
ዋልታ ምሰሶ ነሽ የትግላችን ማገር።
አንቺ የሁሉ እናት ማዘር እናት ዓለም
መላ ሕይወትሽን ሳትሰለች አንዴም
አንዱን አስተምረሽ
ሌላውን አሳድገሽ
ሚቹንም ገንዘሽ
እሹሩሩ ኢሕአፓ ብለሽ
　　　　እንደዘምርሽ
አሁንም መርቂን እደጉልኝ ብለሽ
ቤታችን ኢሕአፓ ያብብልን ብለሽ
አለብሽ አደራ ለኢትዮጵያ ሀገርሽ።
አለብሽ አደራ ለኢትዮጵያ ሀገርሽ።
እናት ዓለም ማዘር
የታጋይ ጓዳ በር።
[http://www.yatewlid.org/images/mp3/Mother_EnatAlem_012707.mp3](http://www.yatewlid.org/images/mp3/Mother_EnatAlem_012707.mp3)